# DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## ማደስ፣ ማጠናከር፣ መልሶ ማደራጀት (RRR)
## የአዲስ ትምህርት ቤቶች ውጥን የተጠናከረ የ ኃይል ሰው አመዳደብ ሞዴል
## ለዲሲፒኤስ

## ተዘውትረው የሚነሡ ጥያቄዎች

- **RRR ምንድን ነው?**
  RRR ለ “Renew. Revitalize. Reorganize.” “ለማደስ፣ ለማጠናከር፣ መልሶ ለማደራጀት” የቆመ ነው። የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችን ለማጎልበት በቀድሞ ጠንካራ ቴክኖሎጂ ላይ በተሠረቱ ሞዴሎች ለትም ህርት ቤቶቻችን አጓጊና አዲስ የትምህርት ፕሮግራሞች ለማምጣት የታሰበ እቅድ ነው። እነዚህን ፕሮግ ራሞች ሥራ ላይ ለማዋል ሪሶርሶቻችንን በሚገባ መመደደብ አለብን።

- **ትምህርት ቤቶችን መልሶ ስለማደራጀት ባለዎት እቅድዎና በ RRR ዎ አዲስ የትምህርት ቤት ፕሮግራም መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**
  አጥጋቢ ዓመታዊ እድገት (AYP) በተከታታይ ማሳየት ባለመቻላቸው የተነሣ ትምህርት ቤቶችን መልሶ የማጠናከሪያ እቅድ እንዲነድፉ ፌድራላዊ ግዴታ የተጣለባቸው 27 ትምህርት ቤቶች በዲሲትሪክቱ ይገኛሉ። አንድም ልጅ ተንጥሎ ወደ ኋላ የሚቀር አይኖርም (NCLB) የተሰኘው ደንብ ለእዚህ ለውጥ አምስት አማራጮችን ያቀርባል። ተከታታይ በሆኑ የማኅበረሰብ ስብሰባዎች ላይ፣ ስለ እነዚህ አማራጮች ምንነትና ለትምህርት ቤቶችም መልሶ በማደራጀት ደረጃ ምን ማለት እንደሆኑ ማብራሪያ እንሰጣለን።

  ከፍ ብሎ የተገለጸው የ RRR እቅድ፣ በጣም በተቀላጠፈና ሥልታዊ በሆነ መንግድ ከፍተኛ ጥራት ያለው፣ ሁሉን አቀፍ አጠቃላይ የአካዳሚክ ፕሮግራም ለተማሪዎች ሁሉ ለማቅርብ እንዲቻል የትምህርት ቤቶችን ሥርዓት መልሶ ለማደራጀት ሀሳብ ያቀርባል። RRR የተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ስኬታማ የሆነ የዲ ሲፒኤስ ፕሮግራሞች በሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዲገመገሙ፣ አሁን ያሉ ፕሮግራሞች እንዲዳብሩ፣ አዲስ ፈጠራዊ አቀራርቦች እንዲመቻቹ የትምህርት ሥርዓቱን በትክክል እንዲመጥኑን በማድረግ ይሳተ ፉል። በተጨማሪ ይህ እቅድ፣ ማኅበረስቡ ኣስተያየት እንዲሰጥብትና ሀሳቦችንም ለማሰባሰብ ተከታታይ የሆኑ የማኅበረሰብ ውይይቶች እንዲካሄድ ያደርጋል።
  .

- **ትምህርት ቤቶችን ለመዝጋት ለምን ያስፈልጋል?**
  ትምህርት ቤቶቻችን በአስፈላጊው ሪሶርስ ተደራጅትው መገኘት በሚገባቸው ሁኔታ አልተደራጁም። አሁን ከምንገኝበት ትነሥተን ልንደርስበት ከምንፈልገው ለመድረስ ሪሶርሱና የሰው ኃይሉ ለማሟላት ምን መልክ መያዝ እንደሚኖርበት የቀየስን ሲሆን፣ ይኸው ሪሶርስ ሁሉ ውጤታማ በሆነ መንግድ ተግባር ላይ መዋሉን ለማስረገጥ ከፍተኛ የሆነ ጉልህ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል። በመሆኑም ልጆቻችን ጥራት ያለው የትምህርት ፕሮግራም እንዲያገኙና እነሱም እንዲረዱ ለማድረግ ትምህርት ቤቶቻችንን ዘግተን ቀስ በቀስ አጠቃላይ ሁሉን አቅፍ የሆነ የስው ኃይል ሞዴል የሚኖራችው ይሆናል።

- ***የትኞቹ ትምህርት ቤት መዘጋት እንዳለባቸው የተወሰነው እንዴት ነው? የተወሰኑባቸው ምስፈርቶችስ ምንድን ናቸው?***
  *እቅዱ የተነደፈው በሁለት ደርጃ ትንተናና በበርካት ምስፈርቶች በመጠቀም ነው። የመጀመሪያው ደረጃ ትንተና፣ ከምዝገባ ማሽቆልቆል እና ከአጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ምዝገባ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጭብጥ መረጃዎችን መርምሯል። በእነዚህ መረጃዎች በመጠቀም፣ ለመዘጋት የታጩ 40 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አዘጋጀን። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ለመጠቆም የበቁት፣ የተደረገው የሂሳብ ስሌት፣ ትምህርት ቤቶቹ ለአለፉት አምስት ዓመታት፣ ያለማቋረጥ ከመካከለኛው የምዝገባ ቁጥር በታችና ከመካከለኛው የምዝገባ መጠን ማሽቆልቆል በላይ ሆነው መገኘታቸውን ካመለከተ በኋላ ነው።*

  *ከዚህ በኋላ ሌሎች ጉዳዮችን ማለትም የጅኦግራፊ ክልልን፣ ለእግር ጉዞ ቅርብና አምቺነት ያለው ሆኖ መገኘትን፣ የምዝገባ ገጽታንና አዝማሚያን፣ ለወደፊቱ ሊፈጠር የሚችለውን የአጎራባቾች ጫናን፣ የቦታ ተስማሚነትን፣ ለሌሎች ትምህርት ቤትች ያልው ቅርበትን፣ እና በዲሲፒኤስ ሥልት ላይ ያለው አጠቃላይ ጫናን የተመለከተ ሁለተኛ ደርጃ ትንተና ተካሂዶል። እያንዳንዱ ነጥብ ከየትምህርት ቤቱ፣ ከየስብስቡ፣ እና ከአጎራባች ክልሎች አንጻር ለማየት ተችሏል።*

  *.ለተማሪዎችና ለትምህርት ቤቶች ሥርዓት የሚሰጠውን ጠቀሜታ ሊያጎለብት የሚችል ተገቢነት ያለው ምክንያትን የተንተራሰ፣ አጠቃላይ ሁሉን አቀፍ እቅድ ለመፍጠር፣ በዚህ ሂደት አማካይነት ጥቂት ትምህርት ቤቶች ከታቀደው ዝርዝር ውስጥ ሲጨመሩ ጥቂት የሚሆኑ ደግሞ እንዲሰረዙ ተደርጓል።*

- ***ይህ እቅድ የመጨረሻ ነው ወይ?***
  *አይደልም። ይህ እቅድ የያዘው መነሻ ሀሳብ ነው። |እቅዱን ለማኅበረሰብ ውይይቶች በማቅረብ ሀሳብ ለማሰባሰብ እንሞክራለን። በጥር ወር መጨረሻ ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ ለማድረግ በውይይቱ ላይ የሚነሡ አስተያየቶችን ከጥናታችን ጋር እናዋሕዳለን።*

- ***ማኅበረሰቡ የሚደመጠው እንዴት ነው?***
  *ማኅበረሰቡ፣ በማኅበረሰብ ውይይቶች ላይ በሚሰነዘሩ አስተያየቶች አማካይንት ሀሳቡ ይደመጣል። በተጨማሪም ስለ እቅዳችን ያለዎትን እስተያየት በዲሲፒኤስ ድረገጽ አማካይነት እና በጽሑፍም ለቻንስለሩ ጽሕፈት ቤት የሚላከውን በደስታ እንቀበላለን። የሚደርሱን አስተያየቶች ሁሉ የመጨረሻው ውሳኔ ከመደረጉ በፊት ከግምት እንዲወሰዱ ይደረጋል። የሚካሄዱ የማኅበረስብ ውይይቶች ዝርዝር ከዚህ ሠነድ መጨረሻ ላይ ተያይዞ ይገኛል።*

- **FAQ *ጥሩ ነው፣ ነገር ግን ዝርዝር እፈልጋለሁ፣ የት ነው ማግኘት የምችለው?***
  *ደረ ገጻችን የሆነው* www.k12.dc.gov *በዋናው ገጽ ላይ እቅዱንና ሌሎችንም ተዛማጅ የሆኑ ጽሁፎችን ማየት ይቻላል። ይህም ከከንቲባ* Mayor Fenty’s *እቅድ እና በእኛም እቅድ ውስጥ ከተካተተው የድጋፍ ምንጭ ጽሁ ፎቹን ያካትታል። ከጊዜ በኋላና ውይይታችንም እየገፋ ሲሄድ ለእያንዳንዱ የህንጻና የቦታ ሁኔታ እቅድን በተ መለከተ በግልጽ ለማስቀመጥ እንሞክራለን። የኢንተርኔት አገልግሎት ለሌላችው ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ በማኅበረስብ ውይይቶች አማካይነት ተጨማሪ መረጃዎች እንሰጣለን።*

  ***የት ነው ተማሪዎች የሚመደቡት?***
  *ተማሪዎች፣ ተገቢ ለሆነው የክፍል ደረጃ በጣም ቅርብ በሆነ አጎራባች ትምህርት ቤቶች ይመደባሉ። በተጨማሪም ከጥር ወር ማለቂያ አንሥቶ መጠየቅ ላለባቸው ወላጆች፣ ከመኖሪያ ክልል ውጪ ዝውውር መስጠታችንን እንቀጥላለን። በ* RRR *አማካይነት ለሁሉም ወላጆች የሚሆን በየቀጠናው ጥራት ያላቸው በርካታ የትምህርት ቤት አማራጮች እናቀርባለን።*

- ***የተለቀቀ ባዶ ሕንጻ አካባቢ መኖር እሰጋለሁ። የትምህርት  ሕንጻ ሲዘጋ ህንጻው ምን ይደረጋል?***
  *ከተማይቱ፣ ህንጻውን መኖሪያ ከማድረግና ከዲሲፒኤስ ፍላጎት አንጻር ተግምግሞ በንብርትነት ተመዝግቦ ይቀመጣል። ትምህርታዊ ፍላጎትን በቀድሚያ በመደገፍ ህንጻዎቹን ለከተማችን ጥቅም ሊውሉ በሚችሉ መንገድ ልንገለገልባቸው እንፈለጋን። ለምሳሌ የትምህርት ቤት ህንጻ የተማሪዎችና የቤተሰቦች የጤና ማዕከል ለማካሄጃ አገልግሎት፣ የለጋ የልጅነት የትምህርት ፕሮግራም ማካሄጃነት ወይንም ለከተማይቱ ሌላ ወኪል ሊሆን ይችላል። ማናቸውም ህንጻ ምንም ሳይሠራበት ለተወሰነ ጊዜ ተቀምጦ የሚገኝ ከሆነ ንብረቱን ጥቅም ላይ ለማዋልና የከተማይቱን ህንጻ ለመጠበቅ አስፈላጊውን ተገቢ እርምጃ እንወስዳለን። ንብረቱን ለመሸጥም ሆነ ወይም ያለ አንዳች ጥቅም ተቀምጦ ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን ፍላጎት የለንም።* .

- **ትምህርት ቤቴ ቢዘጋ መምህራኑ፣ ጠቅላላ ሠራተኛው እና ርእሠ መምህሩ ምን ይሆናሉ?**
  *መምህራኑ ሌሎች የአዲስ ትምህርት ቤቶች ፕሮራሞችን፣ የተማሪዎችን መጠንና ፍላጎቶቻቸውን ማገል ገል እንዲችሉ ሁኔታዎች እንዲመቻችላቸው የየመምህራኑ ፍላጎት ይታያል። መምህራንና ሠራተኛው በየግል የሙያ ማኀበሮቻቸው በሠራተኛ ኮንትራት የዝውውር መብት መሠረት ምርጫቸው ወደ ሆነው አዲስ ፕሮግራም መዛወር ይችላሉ።*

- **ትምህርት ቤቴ የበጎ አድራጎት ቻሮታው ይቀበላል፤ ሆኖም ትምህርት ቤቴ ሊዘጋ ነው። የበጎ አድራጎት ቻሮታው ምን ይሆናል?**
  *በመሠረቱ ቻሮታዎች፣ ከህንጻውች ይልቅ የሚደረጉት ለተማሪዎችና ለፕሮግራሞች ነው። ተማሪዎች የበጎ አድራጎት ስጦታው የሚያካሂደውን ፕሮግራም ማግኘታቸውን እንዲቀጥሉ ቻሮታችንን እየመረመርንና ከቻሮታ አድራጊዎች ጋር እየተነጋገርን ነው።*

- **የተመደቡት ትምህርት ቤቶች የሚዘጉት መቼ ነው?**
  *ውሳኔው አንድ ትምህርት ቤት የመዘጋት ከሆነ፣ ያ የተያዘው ትምህርት ቤት የትምህርት ዓምት እስኪ ያከትም ድረስ ትምህርት ቤቱ አይዘጋም። አብዛኛው ትምህርት ቤቶች ለ* 2008 – 2009 *የትምህርት ዘመን ይዘጋሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ትምህርት ቤቶች ቆይተው ይዘጋሉ።*

| ቀጠና | ቀንትና ጊዜ | ቦታ |
|---|---|---|
| 1, 2, 6 | 12/10<br>6 – 8 ፒኤም | Tubman 1ኛ ደ/ት/ቤት<br>3101 13th St., NW |
| | 12/17<br>6 – 8 ፒኤም | Francis መ/2ተኛ ደ/ት/ቤት<br>2425 N St., NW |
| | 1/9<br>6 – 8 ፒኤም | Miner 1ኛ ደ/ት/ቤት<br>601 15th St., NE |
| 4,5 | 12/11<br>7:30- 9:30 ፒኤም | Noyes 1ኛ ደ/ት/ቤት<br>2725 10th St., NE |
| | 12/18<br>6 – 8 ፒኤም | Barnard 1ኛ ደ/ት/ቤት<br>430 Decatur St., NW |
| | 1/10<br>6 – 8 ፒኤም | Emory 1ኛ ደ/ት/ቤት<br>1720 1st St., NE |
| 7, 8 | 12/12<br>6 – 8 ፒኤም | Patterson 1ኛ ደ/ት/ቤት<br>4399 South Capitol Terr., SW |
| | 12/19<br>6 – 8 ፒኤም | Plummer 1ኛ ደ/ት/ቤት<br>4601 Texas Ave., SE |
| | 1/11<br>6 – 8 ፒኤም | Hart መካከለኛ ት/ቤት<br>601 Mississippi Ave., SE |